የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፵፯
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፮ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

19th Year No. 47
ADDIS ABABA 3rd July, 2013

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፯፻፺፮/፪ሺ፭ ዓ.ም

የዓለም አቀፍ አረንጓዴ ልማት ተቋም ማቋቋሚያ ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ..........ገጽ ፮ሺ፱፻፩

CONTENTS

Proclamation No. 796/2013

**Global Green Growth Institute Establishment Agreement Ratification Proclamation ..... Page 6901**

## አዋጅ ቁጥር ፯፻፺፮/፪ሺ፭

## የዓለም አቀፍ አረንጓዴ ልማት ተቋም ማቋቋሚያ ስምምነትን ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

የዓለም አቀፍ አረንጓዴ ልማት ተቋም ማቋቋሚያ ስምምነት እ.አ.አ. በጁን ፳ ቀን ፪ሺ፲፪ በሪዮ-ዲ ጄኔሮ የተፈረመ በመሆኑ፤

አገራት የአባልነት ማፅደቂያ ሰነዳቸውን የዓለም አቀፍ አረንጓዴ ልማት ተቋም ዋና ዳይሬክተር ዘንድ ማስቀመጥ እንዳለባቸው በስምምነቱ ስለተደነገገ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፬ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የዓለም አቀፍ አረንጓዴ ልማት ተቋም ማቋቋሚያ ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፺፮/፪ሺ፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

## PROCLAMATION No. 796/2013

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT ESTABLISHING THE GLOBAL GREEN GROWTH INSTITUTE

WHEREAS, the Agreement Establishing the Global Green Growth Institute was signed in Rio de Janeiro on the 20th day of June, 2012;

WHEREAS, it is stipulated in the Agreement that the states shall deposit their instrument of ratification with the Director General of the Global Green Growth Institute;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Agreement at its session held on the 11th day of June, 2013;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Global Green Growth Institute Establishment Agreement Ratification Proclamation No. 796/2013".

ያንዱ ዋጋ
Unit price 2.30

www.chilot.me

**፪. የስምምነቱ መፅደቅ**

የዓለም አቀፍ አረንጓዴ ልማት ተቋምን ለማቋቋም እ.አ.አ. በጁን ፳ ቀን ፪ሺ፲፪ በሪዮ ዲ ጄኔሮ የተፈረመው ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**2. Ratification of the Agreement**

The Agreement Establishing the Global Green Growth Institute signed in Rio de Janeiro on the 20th day of June, 2012 is hereby ratified.

**፫. የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ስልጣን**

የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን አግባብ ካላቸው የፌደራል፣ የክልልና የከተማ አስተዳደር የመንግስት መስሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ስልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

**3. Power of the Environmental Protection Authority**

The Environmental Protection Authority is hereby empowered to take, in cooperation with the appropriate federal, regional and city administration government organs, actions necessary to implement the Agreement.

**፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**4. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**አዲስ አበባ ሰኔ ፳፮ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**Done at Addis Ababa, this 3rd day of July, 2013.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ

www.chilot.me